## *የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለመጠየቅ መሟላት ያለባቸው ሁኔ ዎች*

የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት በሚቋቋምበት አካባቢ ላለው ማኅበረሰብ ከሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ሕጋዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በባለሥልጣኑ በኩል ይስተናገዳል፡፡ በመሆኑም የአገልግሎቱን ፈቃድ ለመጠየቅና በአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን በፈቃድ ጥያቄ ወቅት የሚከተሉት መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. አመልካቹ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማኅበር ወይም ድርጅት መሆኑንና ለትርፍ ያልተቋቋመ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣
2. የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎቱ ማኅበረሰቡን የማገልገል ዓላማ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፣
3. ማ በረሰቡ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት እንዲቋቋምለት በጽሑፍና በፊርማው ድጋፍ የሰጠ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፣
4. የአመልካቹን የቦርድ አባላት ስም፣ አድራሻ፣ የትምህርት ደረጃና ፊርማ የያዘ ሰነድ፣
5. ስለአገልግሎቱ መቋቋም የቦርዱ ውሳኔ ያሳለፈበት ቃለ ጉባኤ፣
6. የጣቢያውን የፋይናንስ፣ የሰው ኃይልና የቴክኒክ ሁኔታ የሚገልጽ የፕሮጀክት ሰነድ፣



7. ጣቢያውን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ አቅም የሚያሳይ ማስረጃ፣
8. አመልካቹ ከሚገኝበት ክልል ወይም ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣



*የጅማ ማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ የቦርድ አባላት ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ*



*የአርጎባ ማኅበረሰብ ሬዲዮ የፈቃድ አሰጣጥ ሥነስርዓት*



*የዋግኽምራ ማኅበረሰብ በማኅበረሰብ ሬዲዮ ላይ ከባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ጋር ውይይት ሲያካሄዱ*



## *የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ የት ይገኛል?*

የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የማመልከቻ ቅፅ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ወደሚገኘው የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ኃይለዓለም ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 204 በአካል በመቅረብ ወይም የባለሥልጣኑን ድረ-ገፅ www.eba.gov.et በመክፈት ማግኘት ይቻላል፡፡

## *በባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ፈቃድ የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት*

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 533/99 ከተቋቋመ ወዲህ በርካታ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሰጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ተጠቃሽ ነው፡፡ እስከ አሁን ለ10 የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ዝርዝር መረጃቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**«አንድ ማኅበረሰብ ከምንም ነገር በላይ የሚጠነቀቅለትና የሚንከባከበው ነገር ቢኖር ባህሉ ነው»**

*የማኅበረሰብ ሬዲዮ*
*ፅንሰ-ሐሳቦች*
*የማቋቋም ሂደቶች*
*ሕጋዊ ገፅታዎች*
*2002 ዓ.ም*

## ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ፈቃድ የወሰዱ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያዎች

| ተ.ቁ | የጣቢያዉ ባለቤት | የባለቤትነት ሁኔታ | የተቋቋመበት ዓ.ም | የፍሪ ኩዌንሲ ዓይነት | የስርጭት ሽፋን | የስርጭት ቋንቋ | ሳምን ዊ የስርጭት ሰዓት | ጣቢያው የሚገኝበ ት ከተማ | አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጅማና አካባቢ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2000 | FM 102.0 | አካባቢያዊ | አማርኛና ኦሮሚኛ | 89 | ጅማ ዩንቨርሲቲ ግቢ ውስጥ | በስርጭት ላይ |
| 2 | የኮሬ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 1998 | FM 92.3 | አካባቢያዊ | አማርኛና ኮሬቴ | 21 | አማሮ ልዩ ወረዳ ኬሎ ከተማ | በስርጭት ላይ |
| 3 | የከምባ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2000 | FM 105.8 | አካባቢያዊ | ከምባቲኛ | 58 | ዱራሜ | በስርጭት ላይ |
| 4 | የከፋ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2000 | FM 102.5 | አካባቢያዊ | ከፊኛ | 21 | ከፋ ወረዳ ቦንጋ | በስርጭ ት ላይ |
| 5 | የኮምቦልቻ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2000 | FM 104.8 | አካባቢያዊ | አማርኛ | 33 | ኮምቦልቻ | በስርጭ ት ላይ |
| 6 | የሱዴ ወረዳ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2001 | FM 103.5 | አካባቢያዊ | ኦሮሚኛ | 16 | ኮሬ ኩሉ ቀበሌ | በስርጭ ት ላይ |
| 7 | የዋግኽምራ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2002 | FM 92.7 | አካባቢያዊ | አማርኛ ፤ኽንጢ፤አገውኛ | 30 | ሰቆጣ | በስርጭ ት ላይ |
| 8 | የአርጎባ ማ በረሰብ | የማ በረሰብ | 2002 | FM 98.6 | አካባቢያዊ | አርጎቢኛና አፋርኛ | 33 | አርጎባ ልዩ ወረዳ ጋቺኒ | በስርጭ ት ላይ |
| 9 | የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ | የማ በረሰብ | 2003 | FM 100.5 | ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲና አካባቢው | አማርኛና ኦሮሚኛ | 42 | አዲስ አበባ | ስርጭት ለመጀመር በዝግጅት ላይ |
| 10 | የሰቲት ሁመራ ማኅበረሰብ | የማ በረሰብ | 2003 | FM 106.9 | ሰቲት ሁመራና አካባቢው | ትግረኛ | 98 | ሰቲት ሁመራ | ስርጭት ለመጀመር በዝግጅት ላይ |



የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

### የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
### The Federal Democratic Republic of Ethiopia

### የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን
### Ethiopian Broadcasting Authority

### ፈቃድ የወሰዱ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያዎች ዝርዝር መረጃ

ስልክ /Tel: 251-0115538760/59
ፋክስ /Fax: 251-0115536750
ኢ. ሜይል/E Mail: e.b.a1@ethionet.et
ድረ-ገጽ/Website: WWW.eba.gov.et
የመ.ሣ.ቁ /P.O.Box: 43142

የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ